# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT

جبهة تحرير أورومـــو

G

aafa: 24-04-2012 ibsa تاريخ

Lakk.: 007/-abo/2012 رقم

## *ህዝብን ከህዝብ ማፋጀት ኦሮምያ ውስጥ እየተፋፋመ ያለውን*
## *የጸረ ጭቆና ኣመጽ መቀልበስ ኣይችልም*

### *የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ*

*የወያኔ ኢህኣዴግ መንግስት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ኣነጣጥሮ ከሚያካሄዳቸው የማጥቃት ዘመቻዎች መካከል ኣንዱና ትልቁ ኣንዳንድ የሌሎች ብሄር ብሄረሰብ ተወላጆችን ኣሳስቶ በማስታጠቅ በሁሉም ኣቅጣጫ ኦሮሞ ላይ ማነሳሳት ነው። ኦሮምያ ውስጥ የሚኖሩትንና ከኦሮምያ ጋር የ ዘመናት መልካም ጉርብትና የነበራቸውን የብሄር ብሄረሰብ ተወላጆችን እየመለመለ በማስታጠቅ ኦሮሞ ላይ ያነሳሳል። በዚሁ መልኩ እስከ ዛሬ ድረስ እንደ ሶማሊ (ኢሳ)፣ ኣፋር፣ ጌዲኦ፣ ሲዳማ፣ ኣማራ፣ ቡርጂ፣ ጉሙዝና ሌሎችንም በተለያዩ ጊዜያት ከኦሮሞ ህዝብ ጋር በማጋጨት፣ ኣንዳንዴም እያስታጠቀ ኦሮሞን በማስመታት የሺዎች ህይወት እንዲጠፋና በሚሊዮኖች ብር የ ሚገመት ሃብት ንብረት እንዲወድም ምክንያት ሆኗል።*

*በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በምስራቅ ወለጋ ኣዋሳኝ ኣካባቢዎች ነዋሪ የሆኑትን የጉሙዝ ብሄረሰብ ተወላጆችን ሆን ብሎ በማስታጠቅ በኣካባቢው ሰላማዊ የኦሮሞ ነዋሪዎች ላይ ሲያነሳሳ እንደቆየ ይታወቃል። ለሁለት ኣመታት ሳይቁዋረጥ በተካሄደው የብ ኣጫሪነትና የትንኮሳ ዘመቻ እስካሁን የመቶዎች ህይወት እንደ ዋዛ ጠፍቷል፣ በከፍተኛ መጠን የሚሰላ ንብረትም ወድሟል። ስርኣቱ ሰሞኑንም ይህንኑን የትንኮሳ ድርጊቱን እንደገና በማደስ የመቶዎች ህይወት በተጨማሪ እንዲጠፉ ኣድርጉኣል። የህወሃት ስርኣት ሆን ብሎ በሞርሞር ወንዝ ሸለቆ በመልካም ጉርብትና በጋር የሚኖሩትን የኦሮሞና የጉሙዝ ብሄረሰብ ተወላጆችን በማጋጨት በሚጠፋው የሰው ህይወት ምን ኣይነት ጥቅም ሊያገኝበት እንደፈለገ ለመገምት ኣያዳግትም። ወያኔ በዚህ እኩይ ተግባሩ ሊጠቀም የፈለገው ከፍተኛ የስጋት ምንጭ የሆነበትን የኦሮሞ ህዝብ ሃይል በተቻለለት መንገድ ሁሉ እየሸረሸረ ማዳከምን ነው።*

*የወያኔ መንግስት ይህንን ግጭት እንደገና በማደስ በተለይም ኦሮሞዎች እንዲጠቁ ሆን ብሎ እ ያሴረ የሚገኘው በኦሮምያ የረ ስርኣቱ ትግል ከማንኛውም ጊዜ በላቀ መልኩ እየተፋፋመ መ ያዣ መጨበጫ ባሳጠበት ወቅት መሆኑ ግልፅ ነው። የኦሮሞ ብሄርተኞች ምስራቅ ምእራብ፣ ሰሜን ደቡብ ሳይሉ በተለያዩ ስልቶች እየተደራጁ በስርኣቱ ላይ ትግላቸውን ማፋፋም በመቀጠላቸው ጭንቀት የዋጠው ወያኔ እንደ ኣመሉ ይህን መሰል የቀቢ ተስፋነት እርምጃዎችን ወደ መውሰድ ገባ። የሚታየው የትግል እንቅስቃሴ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እያደገ በመምጣቱ ከ ኦሮሞ ህዝብ ጋር ምንም ኣይነት የጠላታዊነት ታሪክ የሌላቸውን የብሄር ብሄረሰብ ተወላጆችን ኣሳስቶ በማስታጠቅ በሁሉም ኣቅጣጫ ኦሮሞን ማስመታት እንደ መፍትሄ ታየው። በዚህ እንቅስ ቃሴው የህዝብን የትኩረት ኣቅጣጫ ኣስቀይሮ ሁሉም ስርኣቱን መታገል ትቶ እርስ በራሱ ላይ እየተነሳሳ ደም እንዲፋሰስ ማድረግ የወያኔ መንግስት ሴይጣናዊ ምኞት ነው።*

*የኦሮሞ ነፃነት ግንባር የጉሙዝ ብሄረሰብ ተወላጆችን ጨምሮ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ለዘመናት መልካም ጉርብትናና ወዳጅነት እንዳላቸው ለሚታወቁ ህዝቦች በሙሉ ያለው መልእክት ኣጭርና ግልፅ ነው። የወያኔ መንግስት የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የናንተም ትልቁ ጠላታችሁ መሆኑን ኣስ ታውሱ። ዛሬ የግል ጥቅሙን ኣስልቶ ከናንተ በስተጀርባ የቆመ በማስመሰል ኦሮሞ ላይ ሲያነሳ*

ሳችሁ ነገ ደግሞ ተገልብጦ ከኦሮሞው ወይም ከሌላው ህዝብ ጎን ሆኖ ጦር ሊ ያሰብቅባችሁ እንደሚችል ኣትዘንጉ። በናንተና በወንድማችሁ የኦሮሞ ህዝብ መካከል ማንኛውም ኣይነት ኣለመግባባት ቢከሰት እንኩዋ በመልካም ባህላችሁና በጉርብትናችሁ ታሪክ መሰረት ችግሮቻችሁን መፍታት እንጂ በወያኔ መታለል እንደሌለባችሁ ኦነግ ጥሪውን ያድስላችሁዋል። ተመሳሳይ የጭቆና ታሪክ ጠባሳ ያላቸው ህዝቦች በሙሉ ከወንድም የኦሮሞ ህዝብ ጋር ቆመው የጋራ ጠላታቸውን በጋራ መታገል ሲገባቸው በጠላት ተታልለው የኦሮሞ ህዝብ መግረፊያ ጅራፍ መሆን እንደሌለባቸው እምነታችን ነው። ህዝብን ከህዝብ የማጋጨት ኣላማው በኦሮምያ ተፋፍሞ ኣምባገነኑና ጨ ቁዋኙን ስርኣት እየነቀነቀ ያለውን ትግል ለመቀልበስና ብሎም የኦሮሞ ብሄርተኞችን የ ትኩረት ኣቅጣጫ ለማስቀየር መሆኑ እሙን ነው። ይሁን እንጂ ይህ የጠላት ምኞት ከ ቶ ሊሰምርለት እንደማይችል የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በኣፅእኖት ማስገንዘብ ይወዳል።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!
የኦሮሞ ነፃነት ግንባር
ሚያዝያ 24, 2012